# ልዩነቶቻችን ውበታችን የሚሆኑት ሲናስተናግዳቸው ብቻ ነው፤ አለበለዚያ ያወዛግቡናል

በሲውደን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ወጣቶች ንቅናቄ ኮንፈረንስ
እስቶክሆልም 21 አፕሪል 2012

በዩሱፍ ያሲን (ንግግር)

## ልዩነቶቻን መካድ ወይም በሃይል አንድ ማድረግ ፍላጎት

ልዩነቶቻችን ውበታችን ነው የተሰኘው አባባል ብርቄዬ መፈክር ነው።OUR DIVERSITY IS OUR BEAUTY የተሰኘውን የፈረንጅኛው አባባል ትርጉም መሆኑ ነው።በዘመነ ደረግ ተብሎዋል።በኢሕዴአግ ዘመንም ተፎክሮበታል።እንከን የማወጣለት ግሩም አባባል ነው። ምክኒያቱ ጉራማሌነታችን ውበታችን መሆኑ አያከራክርምና።ልዩነቶቻችን ብርቄዬ ጌጦቻችን ናቸው።ጥያቄው እውነት ይህው ግሩምና አቻቻይ መፈክር ተግባራዊ መሆን ይቻላል ወይ ነው በዛሪዬቷ ኢትዮጵያችን።አነጋጋሪና አነታራኪው እነዚሁ ውብ የሆኑትና የሚንኩራራባቸው ልዩነቶቻን ለውዝግብ ምክኒያት እና መነሻ የመሆናቸው ጉዳይ ነው።የማንነት ፖልቲካ መሠረቱ እነዚሁ ልዩነቶቻችን መሠረት አድርጎ ወገን ለይቶ መደራጀትና አንዱ ከእነሱ የተለውን ” ሌለኛ» የተሰኘውን ተፃርሮ መፋጠጥ ነውና።አንዳንድ ጊዜም መግጠም ነው።

በረዥሙ ታሪካችን ልዩነቶቻችን ማስተናገድ ችለናል ማለት አያስደፈርም።ዲሞክራሲ በመሠረቱ የሥልጣንን ውድድር በሰለማዊ መንገድ አስተናግዶ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ተራ በተራ በመራጩ ሕዝብ ይሁንታ መፈራረቅ ነው።በታወቁ በሕግ በተደነገጉ የጫውታው ሕጎች መሠረት። ተወዳደሮ የሕዝብን ይሁንታ ያጣው ወገን ደግሞ ወሳኔውን ተቀብሎ ከሥልጣን ተሰናብቶ ወደ ተቃዋሚ ቦታ መዞር ነው።ጊዜውን ጠብቆ እንደገና ተወዳደሮ የመራጩን ሕዝብ ፈቃጅነት እንደገና መሻት ነው።በሥልጣን ፈርረቆሹ በምርጫ ሳጥን አማካኝነት ብቻና ብቻ ሲሆን ነው እንግዲህ እውነትም ልዩነቶቻችን ተቀበለንንም አስተንግደንም የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ከሥር መገንባት ጀመረናል የሚንባለው። **ልዩነቶቻችን ማኔጅ ማድረግ ግን አልቻልንም፤ በረዥሙ ታሪካችን።**

እውነት ፤እውነት እነጋገር ከተባለ በራዥሙ ታሪካችን ሌሎች በርካታ ያልተሳኩልን ቁም ነገሮች ነበሩ። አሁንም አሉ።**በራዥሙ ታሪካችን ተቋማት ወይም ኢንስቲቱሾችን መገንባት አልቻልንም።የመሠረትናቸውም በተደላደሉ መሥረቶች ላይ ማኖር አልተሳካልንም።**በእዚሁ ረገድ ሌሎቹ እንዳወቁበት እስካሁን አላወቅንበትም።ይህም ያንድ የቁጭታችን ምንጭ መሆን የነበረበት ጉዳይ ነው።እስካሁን ያልተሳኩልን ዓበይት **አለመሳካቶች መካከል ሥልጣንን መግራት** ሌላው ዓቢይ ቁም ነገር ነው።እስካሁን አላወቅንብትም። በተያያዥ ምክኒያት ሥልጣን **ማጋራትም አላውቅንበትም።**ይህ እኛን በእኛታችን የተናውጠን አልባሌ ልክፍት ግን አይደለም።ልሆን አይችልም።ምክኒያቶች አሉት።ፈተሸን፤ ተመራምረን ትክክለኛዎቹ ምክኒያቶቹን ማገኘቱ የእኛ ፋንታ ነው።በተለይም የእናንተው የእዚሁ አዳራሽ የተሰበሰበው የውጣቱ ሓላፍነት ነው።

ብዙ ጊዜ ልዩነቶቻችን ግጦቻችን ናቸው ከሚለው መፈክር አሽጋግረን ልዩነቶቻችን ማስተናገድና ማስተዳደር አልቻልንበትም ብለናል።እስካሁን አላወቅንበትም ማለት ሳይሻል አይቀርም።እነሱን ከማስተናገድና ማኔጅ ካማድረግ **ይልቅ ልዩነቶቻችን ከእነጭራሹ መካዱ ይቀናናል።**እኛ አንድ ነን፤ የምን ልዩነት ደግሞ አመጣችሁብን ማለቱን የሚናዘወትርም አልጣፋንም።በእኛ መካከል ልዩነት የሚፈጥሩት የውጩ ጠላቶቻችን ናቸው በማለት በሌላው ላይ ማላከኩን የሚንመርጥበት ጊዜም አለ ።ጉርማሌነታችን ከእነአካቴው ሽምጥጥ አድርጎ መካድም ብቻ ሳይሆን **በጉልበት እንዲወገዱ ማጣሩ** ሌለኛው አደገኛ አካሄደ ነው።

ይህንን ውብ መፈክር ተግባራዊ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ዲሞክራሲን በቅጡ ለመማማር በቅድሚያ ልዩነቶችን መቀበል ይኖርብናል።»ሌለኛው መቀበል” የዲሞክራሲ ሀ ሁ ነው ይላሉ ጠበብቶቹ።ምክኒያቱ የሌላውን ስብስብ ወይም ግለሰብ ፖሎቲካዊና ሃይማኖታዊ አመለካከት መቀበል አብሮ መኖር የግድ የሚለው ግዴታችን ነው ማለት ያስደፍራል። **ሌለኛው አለመቀበልና አመለካከቶችን ማስተናገድ አለመቻል ራሱ**

**ልዩነቶች ካለመቀበል** በቅርብ የተቆራኘ አካሄድ ነው።በእዚያኑ መጠን በረዥሙ ታሪካች ካልተሳኩልን ቁም ነገሮች የሚደመር ጉዳይ ስህተት ነው። ቢሆንም እኛን በእኛታችን አብሮን የተወለደ የአርባ ቀን እድላችን ግን አይደለም።ምክኒያቶች ይኖሩታል።አሉትም።ተመራምረን ፤ፈተሸን የችግሩ መነሾ ማግኘቱ የእኛ ፋንታ ነው። በተለይም የእናንተው የውጣቱ የቤት ሥራ መሆን ያለበት ተግባር ነው።

ከረዥሙ ታሪካችን ጉራማሌነታችን በግድ አንድ የማድረግ ሙከራዎች ውስጥ ሁለት አብነቶች ብቻ እንመልከት።በመንግሥታዊ ሥልጣን የተደረጉ የጉልበት እርምጃዎች።መላው የሃገሪቷ ሕዝብ በሃይማኖት አንድ ማድረጉ በኢማም አሕመድ ግራኝ በ 1529/1543 ተሞክሮዋል።የዛሬ 480 ገደማ። ብዙ ጥፋት አደረሰ እንጂ የሃገሪቷን ሕዝብ ማስለም ወይም በግድ ሙስሊም እንዲሆን የተደረገው ሙከራ አልሠራም። በ1877 በቦሩ ሜዳ አፄ ዩሃንስ ሙስሊሞችን በሙሉ ክርስትያን ሁኑ ወይም ክስትኑ ብለው በንጉሣዊ አዋጅ ለማጥመቅ የተደረገው ሙካራም አልተሳካም።አዋጁ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ክርስትያን ያልሆነችሁ ደግሞ "ከሃገሬ ውጡ» ነበረው የተባሉት።ከሃገራቸው አልወጡም።የወጡት በኢጋዥ ሃይል ተጠናከረው አዋጅ አስነጋሪውን አስወገዱት።

በቦሩ ሜዳ ላይ ብዙዎቻችን የማናውቀው ሌላው አንድ-አድርጌ አዋጅ ታውጆ ነበረ ።በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሃዶ ቤተክርስትያን ልቃውነት መካከል በአንድ ልደትና በሁለት ልደቶች ወይም በፀጋና በካራ መካከል የነበረው በየሱስ ክርስቶስ ማንነት ዙሪያ ያጠነጠነ ቃኖናዊ ልዩነት በንጉሠ ነገሥቱ አፄ ዩሃንስና በእዚያን ጊዜ የሸዋ ንጉሥ በነበሩት አፄ ምኒሊክ በተገኙበት እልባት ተበጀለት ይላሉ የታሪክ መዛግበት።የሚገረመው ከእዚያ ጊዜ በኋላ የፀጋና የካራ ሙግት እምብዛም የታየ አይመስልም።

ዲሞክራሲ በመሠረቱ ከእኛ የተለየውን "የሌለኛውን» አመለካከት መቀበል ወይም ማስተናገድ የመቻል አካሄድና አግባብ ነው ብለናል።በቅድሚያ የሌላ ግለሰብና ስብስብ ማንነት መቀበልና አመለካከቱን ማክበር ያካትታል።**ባጭሩ ተቻችሎ መኖር መሠረቱ ፤ማገሩና ግርግዳው እሱ ነው።**በዲሞክራሲያዊ አግባብ የመላ የሃገሪቷ ዜጎችን ፍላጎት በትክክል ያከበረ የሥልጣን ፍርሪቆሽ ዋስትና ማረጋገጥ መቻሉም ከእዚሁ መሥረተ ሓሳብ የሚመነጭ ነው።ይህ ብቻም አይደለም።በርካታ ዋና ዋና መግለጫዎችና ታሳቢዎች መጥቀስ ይቻላል። **ፖሎቲካዊና አመለካከታዊ አብዛሕነት(DIVERSITY) መቀበልና ማክበር ሌለኛው መርሕ ነው።** በተጨማሪ ዲሞክራሲ የዜጎቹን ሰብአዊ ሙብቶች መከበር የሚያራጋግጥ ሥርዓት ትድድር በመሆኑ ይህንን ሙብት ለሁሉ መከበሩን ልረጋገጥ ይገባል።

## *ሥልጣንን ከማጋራታችን በፊት መግራት ሊያስፈልግ ነው*

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ለሕገ-አራዊት የዳረገን በረዝሙ ታሪካችን ***ሥልጣንን መግራት አለመቻላችን*** ይላሉ።በኢትዮጵያ ራዕይ 2020 አውደ ጥናት ላይ የዛሬ 8 ዓመት ባደረጉት ንግግር።ፕሮፈሰሩ ሕግ አራዊት የሚሉትን የሥልጣን አጠቃቀማችን ለብዙ ተጨማሪ ችግሮች ዋናው ተጠያቂ አድርገው ያስቀምጣሉ በእዚሁ ሰመጥር ንግግራቸው። በሌላው አባባል ለፕሮፈሰሩ ሥልጣንን መግራት በተቋማት ወይም በኢኒስቲቱችኖችን አዋቅሮ ዘላቅነት ባለው መልክ ከመገደቡ ውጭ ልሆን አይችልም። እንግዲህ የዛሬ 800 ዓመታት ገደማ የኢንግሊዝ መሳፍንትና ባላባቱ በ1215 ማግና ካርታ በተባለው ታላቁ ሰነድ አማካኝነት የነገሡን ሥልጣን የሚገደብ ቀያዲ ሥርዓት መጫን ከቻሉበት የታሪክ ማጋጠሚያ በአሜሪካው ሕገ መንግሥት ማርቀቅ በኩል ታልፎ የምንመለከተው የሰው ልጅ ለሥልጣን ዳር ድንበር እያበጀ እየገራ የመጣበት ረዥም ታሪክ ሂደት ነው የምንመለከተው።የሰው ልጅ የመሠልጣን ታሪክ አንዱ አካል ነው ማለትም ይቻል ይሆናል።

እኛ ግን እስከ 1966 ድረስ "ነጉሡ አይከሰሰ ሰማይ አይታረስ" በየተባለው መርሕ መሠረት በነገሡ ***ሥልጣን ላይ አንዳችም ገደብ ማበጀት አላመቻችን ነው ተቋማትን መፍጠር ያሰናከለው።***ተተምኖ ፤ተገደቦ ፤ ተምጥኖና ዳር ድንበሩ ተለይቶ በሕግ ተደንግጎ ወይም በእውቅና ታውቆ ካልተሰጠ ድረስ ሥልጣን ፍፁማዊ አገዛዝ እንዳሻው የሚጠቀምበት የጉልበት አገዛዝ ውጭ ምንም ልሆን አይችልም። የፈላጭ ቆራጭነቱ ምንጭም ያልተገደበ ሥልጣን ነው። ለኋላቀረነትችንም ዋናው ተጠያቂም ራሱ እሱ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። ሌሎቹ ምክኒያቶች ከጉልበት አገዛዝ ወይም እሳቸው ሕገ አራዊት ከሚሉት የተቀረነጨፉ(ከቅርንጫፍ የተራባ ግሥ) ናቸው አስተምህሮው፤ እኔ እስከገባኝ ድረስ። ፈላጭ ቆራጭነት ደግሞ የዘፈቀደ አስራር ነው።ሉዓም ያልተበጀለትና ያልተገደበ የሥልጣን ግልቢያ ነው ።ኢንስቲቱሽናላዚድ ወይም ተቋማዊ አሰራርና አካሄድ ፀር

ነው።ፀረ ዲሞክራሲ አሠራር ነው።

ማንነት ምንደነው?

ማንነት አንድ ስብስብ እሱን ከሌሎቹ ስብስቦች የሚለዩትን መታዋቂያ መለያዎቼ ናቸው በሚላቸው ተጋሪዮሾች (COMMONNESS) ላይ ተሞርኩዙ ወገንተኛነት yeመፍጠር ክንዋኔ ነው፤ ባጭሩ። በቅርበት ከሚናውቀው የሃገራችን የቅርብ ታሪክ አንድ ምሳሌ እንወሰድ።"ሥልጤ ፤ ሥልጤ እንጂ ጉራጌ አይደለም" ተብሎ ሪፈረንደም ተደረገ፤እስከዚያ ጊዜ ድረሰ ሥልጤ በጉራጌ ማህበረስብ አባልነት ነበረ የሚታወቀው።በራሱም ሆነ በአጎራባች ሕዝቦች።በሪፈረንደሙ ድምፅ ከሰጡት አብዛኛዎቹ ሥልጤ፤ ሥልጤ እንጂ ፤ጉራጌ አይደለም ብለው ወሰኑ ተባለ።እዚህ ላይ ሁለት ቁም ነገሮችን ልብ በሉ። የሥልጤ ማህበረሰብ በሥልጤነቱ ብቻ መታውቅ መሻቱ አንዱ ነው።በጉራጌነት መታውቅ አለመፈለጉ ደግሞ ሁለተኛው ቁም ነገር ነው። የአንዱን ወገንተኛነት መካድን፤ ሌላውን ወገንተኛነት ማስረገጥ አካሄድ ነው የሚንመለከተው።ብዙ ጊዜ ይህ በምናብ የሚከናወን ድርጊት ነው።

ማንነት (identity) በቀላሉ አማርኛ የመለያ መታወቂያ ቢብል ይቀላል። "እነሱ" እና "እኛ" ተባብለው "እኛን» "ከእነሱ» በሚለያቸው ተጋሮዮሾች መግለጫዎች ወይም COMMONESS ፈልገውና ላንዱ ወገን ወገንተኛት መፍጠር።እርግጥ ፅነሰ ሓሳቡ ከእዚህ በላይ ውስብስብና ረቀቅ ያለ ነው።በጣም አቃልዬ እንዳቀርብኩትም ይገባኛል።በርካታ የሰው ልጅ ስብስቦች ወገንተኛነት የሚፈጥሩበት እንጋራለን የሚሉትን የማንነት መግለጫዎች መዘርዘር ይቻላል።በጣም ብዙ ናቸው።እስቲ ላንድ አፍታ ጥቅቶችን እንመልከት፤

1. ያንድ መንደር (ዓዲ) አባልነት

2.**<u>ያንድ ቋንቋ ተናጋርነት</u>**

3.ያንድ ቅድመ አያት ልጅነት

4.**<u>ያንድ እምነት ተጋሪዮሽነት</u>**

5.ያንድ ታሪክ ተጋሪዮሽነት

6.ያንድ የጎሳ አባልነት

7. **<u>ያንድ የትኒክ ግርፕ(ዘር?) አባልነት</u>**

8.ያንድ አህጉር ልጅነት

9. ያንድ ሕዝብ.

10. **ያንድ ሃገር ልጅነት**

11.ያንድ ጠቅላይ ግዛት ልጅነት

12.ተመሳስይ የቆዳ ቀለም ተጋርዩሽነት

**በቀይ** ቀለም ተፅፈው የተሰመረባቸው ልብ በሉ። **በሰማያዊ** ቀለም የተከተበውን ደግሞ አስተውሉ። የተደረደሩት ከበርካታዎች የተጋሪዮሽነት መግለጫዎች የተወሰኑት ጥቂቶች መሆናቸው ነው።እነዚሁ ሁሉ ግን ባንድ ሚዛን የሚመዘኑም አይደሉም።ሚዛን የሚደፉ አሉ።ሚዛን የማደይፉ ተጋሪዮሾች ይኖራሉ።ባንደ ታሪካዊ መጋጠሚያ ሆነን ሲንመለከታቸው።የዘር ወይም ያንድ ቋንቋ ስብስብ ወይም ያንድ እምነት ወገንተኛት ላይ የተመሰረተው "እኛ» እና "እነሱ» ተሰናኝተው መቧደን ነው እንግዲህ የዓላማችን ሕዝቦችን የሚያነታርከው ፤የሚራኩተውና አልፎ ተርፎ ጦር እያማዝዞ የሚያገዳድለው።ገና ዓላማችን ያወዛግባሉ የተባሉትም እነዚሁ አናቋሪ የማንነት መግለጫዎች ናቸው።

## አናቋሪ የማንነት መግለጫዎች

በተጋርዮሾቹ ላይ ተመስርተው "እነሱ» ና "እ»ኛ ተሰናኝተው የሚደረጉ የወገን ለይታዎች ሁሳ ለመራኮት ምክኒያት አይሆኑም።አይደሉምም።የተወሰኑት ማንነት ዙሪያ የሚደረጉ የማንነት ለይታዎቹ ናቸው ለእዚሁ እርከቻ ብቃት ያላቸው። በተልይም የኢትኒሲቲና የሃይማኖት ወገን ለይታ ናቸው ለውዝግብ ምክኒያት የሚሆኑት።አሚን ማዕሉፍ የተባለው ሊባኖሳዊ ፀሓፊ የዛሬ 17 ዓመት በፊት አገዳዳይ ማንነቶች በተሰኘው በፈረንሳይኛ ተፅፎ ወደ ብዙ ቋንቋዎች የተተረጎመው መፅሓፉ ዋናው መልእክቱና ማጠንጠኛው ይህው

ነበረ።Samuel Huntington የተባለው አሜሪካው ፕሮፌሰር ደግሞ ወደፊቱም ለእርከቻው ምክኒያት ሆነው ዓላማችን ሊያቀራቁሱ የሚችሉት እነዚሁ ሁለት ማንነቶች መግለጫዎች ናቸው ብለው ተነብየዋል፤ ከመሞታቸው በፊት።

## ለመሆኑ ማንነት ለውዝግብ ምክኒያት የሚሆነው መቼ ነው?

ማኅበራዊ ስብስቦች ባንዱ ወይም በሌላው በተጋሪዮሽ መቧደናቸው ወይም ወገን መለየታቸው ሳይሆን የሚያውዛግባቸውና የሚያናታርካቸውና ጦር የሚያማዝዛቸው ነገር ግን ባንድ ርእስ ጉዳይ ዙሪያ አለመስማማታቸው ነው እንጂ።ግለሰብ ለግለሰብ ቡደን ለቡደን የሚያወዛግበው ባንድ ጉዳይ ሆድና ጀርባ ሆነው የሚጋጩት አንድ ጥቅመ ጥቅም ወይም የሚይያምኑበት እሴት አልጣጣም ሲላቸው ነው ይሉናለ፤ የሕብረተሰብ ተመራማሪዎች።

## ለመሆኑ ውዝግብ ምንደነው?

መልስ ማገኘት ያለበት ጥያቄ ነው።

ማንነት አንዱ ስብስብ "እነሱ" ከሚላቸው በተፃረረ አልፎ ተርፎም በተፋጠጠ መልኩ ራሱን የማስቀመጥ (Identify) ክንዋኔ ነው እስከ ተባለ ድረስ ቢዘገይም ወደ ግጭት መመራቱ አይቀሬ ነው የሚመሰለው። ማንነት ሁለት መጠንጠኛ አለው።አንደኛው በተመሳሳይነት ላይ የተመሰረት ተጋርዮሽነትና ዝምድና እንደ ስብስብ ላንድ ወገን ማረጋገጡ ሲሆን፤ሌለኛው ደግሞ ይህንኑ ማረጋገጡ ተግባር የሚከናወነው ከሌሎቹ ወይም "እነሱ" ከሚሏቸው በተፃራርነት ተሰልፈውና ቆመው ነው የሚለው መመርኮዣ ነው።በተጋርዮሾቹ ላይ ተመስርተው "እነሱ» ና "እኛ» ተሰናኝተው የሚደረጉ የወገን ለይታዎች ሁላ ለመራኮትና ለመጋጨት ግን ምክኒያት አይሆኑም ብለናል።አይደሉሙም።አንዱን ስብስብ ከሌለኛው ጋር የሚያጋጨው ግን እነሱና እኛ ተባብለው ልዩ በሚያድርጋቸውና ከሌላው በሚላያቸው ተጋሪዮሽ አንድ ዙርያ በወገንተኛነት መሰብሰባቸው ወይም አልፎ ተርፎ መደራጀታቸው አይደለም።ባንዱ ወይም በሌላው ርእሰ ጉዳይ ወይም ቁም ነገር ላይ መነታረካቸው ወይም አለመስማማታቸው እብለናል።አንዱ የሌላው ዓላማ ግብ እንዳይመታ ለማድረግ ሲፋጠጡና ግጭት ውስጥ ሲገቡ ነው፤ በመካከላቸው ውዝግብ ተፈጥረ የሚባለው። በሕብረተሰባችን በባህላዊ ትረካ መሥረት ምሽትና ርስት ጦር ያማዝዛሉ።አፋርና ኢሣን በወሃና በግጦሽ ይቆራቆሳሉ።ከቤተ ሰብ ጭቅጭቅ ጀምሮ እስከ አተረማማሹ የሶማሌያው እርስ በእርስ ጦርነት ሁሉ በውዝግብ ምድብ ውስጥ ነው የሚካተቱት፤ በውዝግብ አጥኚዎቹ።ለበርካታ ዓመታት መፍትሔ ያላገኘው የዓረብ የእስራኤል ውዝግብ አንዱ ምሳሌ ነው።የሚጋጩትም ባንድ መሬት ባለቤትነት ዙሪያ ነው። የዘመኑ የኢራንና የእስራኤል የኒዩክሌር ባለቤትነት የውዝግብ ሌላው ምሳሌ ነው። አልፈቅድም፤ አደርገዋለሁ የመተላለክ ፍጥጫ ምሳሌ ነው።

# ብሔርተኛነት ምንደነው?

በቀላል አማርኛ ብሔርተኛነት አጠቃላይ በመንግሥት አመሠራረት ዙሪያ የሚነሱ ውዝግቦች መግለጫ ነው። ብሔርተኛነት ከመንግሥት ውጭ ሊታይ አይችልም።አንድ ስብስቡ የራሴ ናቸው የሚላቸውን አባላት ባንድ መንግሥት አሃድ ወይም ትድድር ሥር እንዲጠቃለሉት ምኞቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያደረገው እንቅስቃሴ መግላጫ ተደረጎ እስከ ተወሰደ ድረስ ከፖሎቲካዊ ክውን ወይም አሃድ ውጭ ከቶ ሊታሰብ አይችልም። ከመንግሥት ወይም ከብሔር ማቀፍ ውጭ ብሄርተኛትን ማሰቡ አስቸጋሪ የሚደረገው ይህ ይመስልኛል።ማኛውም ባንድ ስብስብ ዙሪያ በወገንተኛት የተሰለፈ ሃይሉ ሁላ ብሔርተኛ ልሰኝ መቻሉ ግን አጠያያቂ ነው።ምክኒያቱ በማንነቱ በወገንተኛት የተረጃ ሃይል ሁሉ የራሱን መንግሥት ወደ መመሥረቱ አይመራም

ከላይ በሥልጤ ብሔረሰብ መሳሌነት የተመለከትነው ወገንተኛነት ዓላማውና ግቡ ሥልጤን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የራስን ፖሎቲካዊ አሃድ የመስረት ግብና ዓላማ አልነበረውም።የለውም።ይትወሰኑ ስብስቡ ጋር የተያያዙ የአስተዳደር ጥያቄዎችና ችግሮች እልባት እንዲያገኙ መፈለጋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ። ብሔርተኝነት

እንደ ማንነት ማደራጃ፤ ብሔርተኛነት እንደ ስሜት ፤ብሔርተኛነት እንደ እንቅስቃሴና ብሔርተኛት እንደ ኢድዮሎጂ  በብዙ ትርጉም፤ፊቺና ደርዝ ያለው ማስገንዘቢያ ንባበ ቃል ነው።ወደ እነዚህ ዓይነቱ ዝርዝር ገብተን አንዘልቀውም። ስብስቦችን የሚፋጥጣቸውና ግብግብ የሚያስገጥማቸው ተጋሪዮሽነቱን መሰረት አንዘልቀውም።

## የሥልጣና የሃበት ክፍፍል

አንድ ሃገር ውስጥ የተካተት ማሕበረሰቦች በአብሮነት ለመኖር ከወሰኑ በኋላም  የሥልጣንና የሃብት ክፍፍል ደርሻ-ድርሻ ላይ ዓላማዎቻቸው ተፃራሪ ከሆኑ ይፋጠጣሉ። መንግሥቱ የተለያዩ ስብስቦችን የሚያቀፍ ከሆነ ያብሮነት አኗኗራቸው እንዴትና በምን መልኩ ያበጃጁት በሚለው ላይ የግድ ስምምንት ያስፈልጋል። የአናሳዎች የሙብት አከባበርም  ያሿኩታል።አንዱ ክፍል ወይም ስብስብ በኃሳ  ጉልበት በላይነት በተቆናጠጠው ሥልጣን ፍላጎቱን ብቻ በሌሎቹ ላይ ለመጫን ከሞከረም አብሮነቱ አስተማማኝ መሠረት ላይ ተገነባ ማለት አይቻልም።
ላለፉት 20 ዓመታት በኢትዮጵያ የምንመለከታቸው የብሔረሰብና የሃይማኖት አለመግባባቶች የገዢው ፓርቲ የራሱን የሥልጣን እድሜ ማራዘሚያ አድርጎ የተከተላቸውን ፖሊሲ ውጤቶች ናቸው መባሉ የተወሰነ እውነተኛነት ያለው አባል ነው። በከፊል ገዢው ፓርቲ የተከተለው አግላይ ፖሊሲ ውጤቶች ናቸው።ገዢው ፓርቲና መንግሥት በተከተለው አካሄድ ቅርንጫፍ የብሔረስብና የሃይማኖት ማንነቶቻችን ቀዳሚው ሥፍራ ተቆናጥጠዋል። በእዚህ ምክኒያት የቋንቋ፤ የብሔረስብና የሃይመኖት ልዩነቶቻችን አለቅጥ ሰፍተዋል ፤እድሜ ለዚሁ አካሄድ።የጋራ እሴቶቻችን ኮስሰዋል።የሚለያዩን የማንነታችን መግለጫዎች ሁሉ ተጋነዋል። የሚንጋራቸው አሳባሳቢ ማንነቶቻችን ተደፍጥጠዋል።የጎሣ፤ የብሔረሰብና ያንድ እምነት አባልነታችን ገዝፈው እንዲጎሉ ተደርጓል።የሕብረተሰቡ አገኛኝ ጥልፍልፍ ሁሉ እንዲበጠስ ሞከራዎች ተደርገዋል።እነዚሁ ሁላ አንድ አናሳ ቡደን በራሱ አካባቢና ስብስብ ስም የተቆጣጠረውን ሥልጣንና የሃብት ምንጭ የሥልጣኑ እድሜ ማራዘሚያ ማደርጉ  ሃላፍነት የጎደለው አካሄድ ነው።
 በዘመነ መስፍንት አንድ አካባቢ መስፍን የሌላውን መሬት በዘመኑ አባባል “ሃገር” በመደረብ ሌላውን መስፍን ያስገበረ ነበረ።ካስገበሩ በኋላ ጦር  ይመለመሉ እንደሆነ ነው እንጂ በብሔረሰብ መልክ ራሱን አደራጅቶ ሥልጣንን ካንድ ስብስብ በወጡ በኤሌቶች ስም ተቆጣጥረው አያውቁም።አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዩሃንስ ይህንን ማድረግ የሚያስችላቸው ሆኔታ በፍፁም አልነበረም።አፄ ምኒሊክ በደቡብ፤ በምሥራቅና በምዕራብ ባደረጉት የመስፋፋት ዘመቻዎች እርግጥ ከሸዋ አብረው ለዘሙቱት ለሸዋ ዘመኞች ያዳላ አካሄድ ነበራቸው ።በገበሩት ሃገሮች አዲስ ሰፋሪዎች አስፈረዋል።አንዳንድ ጊዜም የሃገሬ ሕዝብ ከመሬታቸው በማፈናቀል።

ስብስቦች እየራስ ራስ መንግሥታት ከመሰረቱ በኋላም የጠብ መነሽ አያጡም፤  በድንበር አከላለልም ሆነ በብሔራዊ ጥቅማ ጥቅሞችን አስመልክቶ ይጋጫሉ። ጥሩ አስረጅ ምሳሌ መሆን የሚችለው በቅርቡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ የራሷን መንግሥት ከመሰረተች በኋላ ጭምር የተቀሰቀሰው ደም አፋሳሹ ጦርነት ነው። ሰሞኑ በሁለቱ ሱዳኖች መካከል የምንመለከታቸው ቁሩቁሶችም ተመሳሳይ ናቸው።

## ብሔረሰብና ሃይማኖት እንደ ማተረማመሻ እቅድ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያችን የብሔረሰብ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ እምነት ተከታዮች መካከል ሃይማኖትም የውዝግብና የማናቆሪያ መነሻ ልሆን መቻሉን ግንዛቤ የብዙዎቻችን ስጋት እየሆነ ከመጣ ስንበትበት ብሎዋል።።በቂ ፍንጮችም ብቅ ብቅ እያሉ ናቸው።
ይባስ ተብሎ በሥልጣን ያለው መንግሥት ሆን ብሎ ልዩነቶቻችን እንድሚያሳ ተመልከተናል።በብሔረሰቦች መካከል በሚነሱት ቅራኔዎች ላይ ቢንዚን ሲያርከፈክፍ ይታያል።ይህ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

## ሕዝባዊ መነሳሳትን ስኬታምነት የሚወስኑ ታሳቢዎች

 ቁንጮ ዲከተሮችንና ገዢ አውራ ፓርቲዎችን ባለታሰባና ባልተጠበቅ አኳኋንና በፍጥነት ሲያስወግዱ የተመለከተነው በቅርቡ በዓረቡ ዓለም የተቀጣጠለው ሕዝባዊ መነሳሳትና እምብተኛነት ለመሳካቱና ወይም ለመንገዳገዱና ወይም ከእናካቴው ለመደናቀፋቸው ተደጋግሞ ከሚጠቀሱት ታሳቢዎች አራቱን ታሳቢዎች

እንመልከት።

1. **የፍራቻ ቆፈንን በቅድሚያ ማሽቀንጠር**
2. **የሠራዊቱ አቋም**
3. **በሕብረተሰቡ ስብስቦች መካከል ያለውን ጤናማ ግኙኝነትና**
4. **የውጩ ሃይል ጣልቃ ገብነት**

በግንባር ቀደም የሚጠቀሱ ናቸው።

በሃገራችን የፍራቻ ቆፈን የመግፈፉ ሂደት ቀስ በቀስ ነገር ግን በእርግጠኛነት እየተካሄደ ነው።የሠራዊቱ አቋም በአመዛኙ ያልውን ሥርዓትን ከድተው በተቃውሚው ወገን ጎን ይሰለፋሉ የሚለው ተስፋ የመነመነ ነው ቢባልም ቅሉ ሙሉ በሙሉ የተሟጠጠ አይደለም። በፊት በሊቢያ አሁን ደግሞ በሶሪያ እንደሚንመለከታው በዓለም ሕብረተሰብ ስም የውጩ ሃይሎች ጠቃገበነት ወሳኝነት ነበረው።በሃገራችን አሁን ባለው ተጨባጭ ሆኔታ ይህ ፋክተር ለጊዜው ከግምት ውጭ መደረግ ያለበት እሳቤ ነው።ምክኒያቱም ግልፅ ነው። በእነዚህ ሃይሎች እይታ በሥልጣን ያለውን መንግሥት አራጋጊ ሃይልነት ነው ጎልት የሚታያቸው።በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ለውጥን ለማገዝ ከተቃዋሚዎች ጎ የመሰለፋቸው ጉዳይ በግምት የሚወሰድ ልሆን አይችልም። ሰለእዚህ ለመነሳሳቱ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በሕብረተሰብ ከዋኝ ስብስቦች መካከል የሚፈጠረው ትብብርና የትግል አጋርነት ነው።ለእዚሁም ነው ሳይውል ሳያድር እነዚህ ሃይሎች ከመቀራረብ ዘልቀው ያለ የሌለ ሃይሎቸውን በማስተባበር መደጋገፍ አለባቸው የሚባለው፤ ተደጋግሞ ተደጋግሞ። ባንድ ላይ ተጣምረው መታገል ነው የጊዜ ጥሪ የሚሆነውም ለእዚሁ ነው።በጥቃቅን ልዩነቶቻቸው ላይ በመቆዝም ከመነታረክ።ገዥው ፓርቲና በሥልጣን ያለው መንግሥት ይህንን በሚገባ ይረዳሉ።ስብሰብ ብለው እሱን ለመግጠም በተዘጋጁ ቁጥር የማተርማመሻ ንድፎች ይቀስላቸዋል።አንድ ጊዜ በብሕረሰብ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሃይማኖት ይከፋፍላቸዋል።የሰሞኑ የጉራ ፋርዳ ባንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያነጣጠረ ማፈናቅል ለእዚሁ ዓይነተኛ ትኩረት ማስየሪያ ምሳሌ ነው።

## ማጠቃሊያ

የዲሞክራሲ ለውጥ ሂደት በተለያዩ ሃገሮች በተለያዩ አካሄዶች ተጠናቅቆቃል።ከበርሊን ግርግዳ መፍረስ በኋላ በምሥራቅ ኤውሮፓ የተካሄድበት አግባብ በላቲን አሜርካ ሃገሮች ከተካሀደበት አከናወን ከሥር መሠረቱ ይለያል።በ1990ዎች መባቻ በምዕራብ አፍሪካ ሃገሮች የተደረጉት የብሄራዊ ኮንፈረንሶች አካሄድ በቅርቡ በዓረቡ ዓለም ከተቀጣጠለ ሕዝባዊ መነሳሳት ጋር ፈፅሞ ተመሳሳይነት የለውም።
የማይባሩ ጦርነትችና ቁሩቁሶች የእዚህ ውጤቶች ናቸው።በሥልጣን **ያላው መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ልዩነቶቻችን ከማስተናገድና እንዲጠቡ ከማድረግ ይልቅ ለሥልጣኑ እድሜ ማራዘሚያ ሆን ብሎ እንዲሰፉ መደረጉን ግልፅ ከሆነ ቆይቶዋል።**በብሔረሰቦችና በሃይማኖች መካከል ያለው ዝምድና ለጋራ ትግልና መደጋገፍ የሚያስካ ደረጃ ላይ እንዳልሆነ መቀበል ነውርነት የለውም።
ለማጠቃልል ፤ከላይ የ ውይይት መንደርደሪያ መጠንጠኛ ያደርግኋቸው ማንነት፤ ወዝግብ፤ ብሔርተኛነትና የመሳሰሉ ፅነሰ ሓሳቦችና ማስገንዘቢያ ንባበ ቃሎች ባለ ብዙ ፊቺ፤ቱርጉምና ፈረጀ ብዙ ናቸው። በ20 ደቂቃ ንግግር ተዛምዶቸው፤ ተያያዥነታቸና ተዋስቦቸው በሚገባ አብራራለሁ የሚል የተሳሳተ ግምት የለኝም። እንደጋን እንደንስብባቸው ኮርኮር ማደረግ ከቻሉ ሙከራው ከንቱ ልፋት አልነበረም እላለሁ።
እንደተመለከትናቸው ልዩነቶቻችን በርካታ ናቸው።ማስተናገድ እንጂ መካድ ወይም በግድ አንድ የማድረጉ ሙከራዎች የተፈለገውን ውጤት እንደማይሰጡ መገነዘቡ የግድ ይላል።**በተለያዩ የሕብረተሰባችን ክፍሎች በቋንቋ፤ በዘር ፤ በበሕረሰብ ወይም በለፈው ታሪክ አተረጓጉምና በወልና በቡደን መብቶች ዙሪያ የሚያነታርኩን ቁም ነገሮች ላይ አሁን አሁን የተያያዘው ውይይት በምር እንቀጥልበት። በተለያዩ መነገዶች የተለያዩ የተቃዋሚ ሃይሎች በየፊናቸው የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪዎች የጋር መግባባት ለመፍጠር ያላቸው ሚና ወሳኝ ነው።ጊዜው መደማመጥን ይጠይቃል።መጠላለፍን ይኮንናል።**
ወደ አዲሶቹ አድማሶች ለመገስገስ አዋሃጅና አሰባሳቢ የሆነ ብሄራዊ ማንነት ለመቅረጽ የሚናድርገው ሙከራ የግድ የሚላቸውን በቅድሚያ ቤታችን የማስተካካል ተግባር አለ።የሁሉም ማንነቶች አቃፊና ደጋፊ የሆነውን

ያንድሃገር ልጅነት (የዜግነት)እንዲሰርፅ ማስፈለጉ የሚያከራክር አይመስለኝም።በተጋሪዮሾቹ ውስጥ ያንድ ሃገር በሰማያዊ የተፃፈው እንበለ ምክኒያት አልነበረም።የተመለከትናቸው አነታራኪ የሆኑትን የቅርንጫፍ ማንነቶችን ሁላ አዋህዶ
ለዘለቄታው ልያስተሳስረን ብቃት ያለው እሱ ብቻ ነው።ባጭሩ ለእሱ አፅንኦት እንስጠው ነው ዋና መልእክቱ።

**ከሩቁና ከቅርቡ ታሪካችን ትምህርት መቅሰም ሌለኛው የቤት ሥራችን ነው።**ስህተቶችን አለመድገም ነው። በሥልጣን ያለው ፓርቲና መንግሥት ለአተረማማሽ ንድፎች ራሳችን አናመቻች።
ከቅረቡ ጊዜ ወደህ እየፈነጠቁ የመጡ የተስፋ ጭላንጭሎች አሉ።በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል ከላይ በተመለከትናቸው አነታርኪዎቹ ርእሰ ጉዳዩች ዙሪያ የጋራ ግንዜቤ እንዲሰረፅ በመሃል መንገድ የመተቃቀፍ ሞከራዎች ይታያሉ።በሃገሪቷ አንድነት ፤ በታሪክ አገነዛዘብ፤በግለሰብና በቡድን መብቶች መካከል መኖር ያለበት ምጥጥን ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ እየተገኘ በመምጣት ላይ ነው።ባጭሩ ለአብሮነታችን አዲስ ቀመር የማገኑት ጅማሮ ላይ ነን።ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ገና ብዙ ይቀረዋል።አሁንም የወደፊቱ አብሮነታችን በምን መልኩ ይደረጅ በሚለው ሓሳብ ላይም የሁሉም ስምምነት ገና አልታከለም ።ይህ ብዙዎቻችን ከእንቅልፍ የሚያባንን የስጋት ምንጭ ሆኖዋል።
የሁሉም ስምምነት የተከለበት ባንደ መንግሥት ሥር በአብሮነት የሚያኖረን ፎርሙላ ገና ያለተቀበሉ ወገኖች አሉ፤ በመካከላችን።ያለፈው የእዚች ሃገር ማዕከላዊ መነግሥት የተመሥረተበትና የተደላደለበት ሂደት ላይ ስምምነት የለም።ከእዚበፊት በሥልጣን ኤሊቶች መካከል ከተደረጉ ጊዜያዊ መሽነጋገሎችን የዘለለና የመጠቀ መሆን ይኖርበታል ያሁኑ ሽርክና።አሁን የሚደረጉ ስምምነቶች እንደ ውበትና ጌጥ የምነመለከታቸውን አብዛሕነታችና ጉራማሌነታችን ወይም DIVERSITY ለማስተዳደር የምንችልበትን ፎርሙላ ማገኘቱ የሚያረጋግጡና ዋስተና የሚሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል። ቀለል ሥራ አይደለም ፤ ግን ይቻላል።ከጉንጭ አልፋ የቃላት አንካሴ(PLOMICS) መወራወሩ ባሻገር በጋራ እነዚህ የጋራ ግንዛቤዎች ለመቅረፅ ተግተን እንሥራ። የኢትዮጵያ ለውጥ ፈላጊ ተግዳሮቶች በአንድ አድርገን ፀሎት መፍትሔ ማገኘት እንደማችል ግልፅ ነው። ልዩነቶቻችን በቅጡ ማስተናገድ ያልቻልንበት ምክኒያቶቹ ተፈለገው፤ተመርምረው መፍትሔዎች የመፈለጉ ጥረት በምር መያያዙ ነው ፍቱን መድሓኒቱ።ልክ ሌሎቹ እንዳወቁበት እኛም እንወቅበት ነው ዋናው መልእክቴ። ይህ አሁንም በወጣቱ ትከሻ ላይ የወደቀ ትውልዳዊ ሓላፍነት ነው።ሁሉ የራሱን የራሱን ሚና መጫወት ቢኖርበትም ትልቁ ድርሻ የእናተው ነው። የእዚህ አዳራሽ ያላችሁ ወጣቶች ማለቴ ነው።ይህንን ሓላፍነት እንደሚወጡትም ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለኝም።

**አመሰግናለሁ!!!!**